# ባገር አንድነትና በባህር በር ጥያቄ ላይ
# እኔም አማራ ነኝ!

ባለንበት ወቅት ስላገር አንድነትና የባህር በር ጉዳይ የሚገደው የአማራ ብሄር ወገን ነው የተባለ ይነገራል። ከሌላው ወገን እንዲሁ በተመሳሳይ መልኩ የሚጨነቅ ኢትዮጵያዊ ቢኖርም እንደ የአማራው አይነት ግን ብዙ ሲባል አንሰማም። የሚባለው ምን ያህል እውነት ነው የሚል ጉዳይ ላንባቢው ትቼ እነዚህ ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች ካገራችን ጥቅምና ጉዳት አንጻር ብናያቸው መልካም ነው። አገራችን አንድነትዋ ቢጠበቅና የባህር ወደብ ቢኖራት ጥቅሙ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ እንጂ ላንድ የተወሰነ ጎሳ ወይም ብሄር እንደማይሆን እሙን ነው። እንግዲህ እንደሚባለው አማራ ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች መታማቱ እንከን አላገኘሁበትም። ምክንያቱም ያገራችንን ክብርና መሰረታዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ካለው እምነትና አላማ የመነጨ አስተሳሰብ እንጂ ሌላ ምስጢር የለውም።

የኢህአደግ መንግስት ትልቁ ስህተት ባገር አንድነት የተከተለው ፖሊስና በአሰብ ወደብ የይገባኛል ጥያቄ ነው። ከዛ ውጭ ያለው ችግር በሂደት የሚቀረፍ እንጂ በተአምር የሚወገድ አይሆንም። የምንመኘው እድገትና ብልጽግና እውን የሚሆነው ለዛ ጉዳይ መክፈል የሚገባንን መስዋትነት ስንከፍል ብቻ መሆኑን መታወቅ አለበት።

ኢህአደግ አንድ ህዝብ አንድ ዓይነት ቋንቋ ስለተናገረ ብቻ በሁሉም ነገር አንድ ነው የሚል እምነት አለው። ይህ አባባል ትክክል ቢሆን ኑሮ በሶማሊያ የምናየው የማያባራ የእርስ በርስ ጦርነት ባልተከስተም ነበር። በኤርትራና ትግራይ ያለው ደገኛው ህዝብ በብዙ ነገር ይመሳሰላል ነገር ግን ያለው የስነልቦና አስተሳሰብ ለየብቻ ነው።ለዚሁ ነው የክልል አስተዳደር የሚባለው ጉዳይ ኢትዮጵያን እየጠቀመ ሳይሆን ጉዳቱ ያመዘነ ነው የሚባለው። ግልጽ ለማድረግ በዚሁ ፖሊሲ ምክንያት ባገር ማሰቡ ትተን ወደየብሄራችን በመውረድ ታላቅዋና ባለታሪክዋ አገራችን እየረሳናት የምንሄድ ያለን ይመስለኛል።እኔ እስከማውቀው ድረስ ብሄር የሚለው ቃል ከግዕዝ የመጣ ሁኖ የግዛት ክልልን አመልካች እንጂ እንዳሁኑ እንደሚባለው ዘርን አያመለክትም። ባገራችን የፊደል መፅሃፍ አሳታሚ የነበሩትን የማያውቅ የለም። የት አካባቢ እንደሆኑ ሲገልፁ "ተስፋ ገብረስላሴ ዘብሄረ ቡልጋ" የሚል የደራሲው ስም ያስቀምጡ እንደነበር አስታውሳለሁ። ይህ ማለት ደግሞ ቀያቸው ወይም የተወሉድበት መንደር የት እንደሆነ ለመንገር የተጠቀሙበት እንጂ ስለዘራቸው ማንነት ለመግለፅ አይደለም። ይህ ያልኩበት ምክንያት ለምሳሌ በትግራይ እንደነ ኩናማና አገው እንዲሁም ሳሆ የሚባሉ አናሳ ወገኖች አሉ። በተመሳሳይ መልኩ በጎጃም ውስጥ ካማራ ወገን በተጨማሪ የኦሮሞና አገው ብሄረሰቦች ያሉበት ክፍለ ክልል ነው። እና ባገራችን ታሪክ በድሮ ነገር ወይም ባሁኑ ማለት ነው ከትግራይ ነኝ ወይም ጎጃሜ ነኝ ሲል ጠቅላይ ግዛቱን ወይም ክ/ሃገሩን እየነገረ ነው ያለው እንጂ ዘሩ ምን እንደሆነ ካለራሱ በስተቀር የሚያውቅ የለም ለማለት ነው።

የራስ ዕድል በራስ መወሰን መብት የሚለው ችግሩ ከፅንሰ ሃሳቡ አይመስለኝም። እንቅፋት የሆነው ያለው መንግስት የስልጣኑን እድሜ ለማራዘም ሆን ብሎ የሚጠቀምበት እንጂ እንደ ሚባለው ፍትህና ዲሞክራሲ በጭቁን ብሄረሰቦች ለማንገስ አለሞኑን በተግባር እያየን ነው። በስማቸው የሚማልላቸው ብሄረሰቦች ያካባቢው ቋንቋ

የሚናገር ገዢ ተቀየረላቸው እንጂ ሌላ ያገኙት ነገር የለም። የሚገርመው የራስ ዕድል በራስ መወሰን የሚለው መርህ እንካን ስናየው ለሁሉም በኩልነት የተሰጠ አይደለም። ለምሳሌ በደቡብ ኢትዮጵያ ብዛት ያላቸው ብሄረሰቦች የደቡብ ህዝቦች ተብለው ተጣምረው ባንድ ክልል ሲጠሩ እናያለን። እንግዲህ በመሃላቸው ሰፋ ያለ የባህልና ልማድ ነገር እንዳለ ይታወቃል። በሌላ ወገን ወደ ሰሜን ያለው ትግርኛና አማርኛ ተናጋሪ ወገን በብዙ ነገሩ አንድ የሆነ ህዝብ የሰሜን ህዝቦች ተብሎ ለምን የክርስትና ስም እንዳልወጣለት ለምን ይሆን ብለን ብንጠይቅ መልሱ ምን እንደሚሆን አላውቅም። አንድነት ላማራ ብቻ የሚጠቅም ይመስል ይህንኑ ሲነሳ የመንግስት ደጋፊዎች ጉዳዩ በጥልቀት ከማየት ይልቅ ወደ ምንም ያልፈየደው ነፍጠኛና ትምክህተኛ የሚባሉ የመሸሻ ቃላቶች ለመጠቀም በፍጥነት ማርሽ ሲቀይሩ ይታያሉ።

ወደ ወደብ ስመለስ ደግሞ የሚከተለውን ለማለት እፈልጋለሁ። በኢትዮጵያና በኤርትራ ያለው ችግር ታሪክና ገዢዎች የፈጠሩት እንጂ የሁለቱ ወገን ህዝብ ሆን ብሎ የሰራው/ያመጣው አይደለም። እና በሁለቱ አገሮች ያሉ ህዝቦች ከጥቅም በላይ ማለትም እኛ ኢትዮጵያውያን ከወደብ በላይ ህዝቡ እንደሚበልጥብንና ወንድማችን መሆኑን ብናሳየው፡ ከመረብ ምላሽ ያለው ህዝብ ደግሞ በተመሳሳይ መልኩ አገራችን ከኢኮኖሚ ጥቅም አንጻር ባያዩዋትና ከልብ ኢትዮጵያ የኛም ናት የሚል አመለካከት ቢያጎለብቱ ለሁላችን መልካም ይሆን ነበር። ከዚያ በመለስ ያለው ግን እኔ እንደ ዜጋ በኢትዮጵያ ትርፍ እንጂ በሌላ ወገን ጥቅም ማሰብ አልችልም። ለብዙ ሺህ አመታት በይዞታችን የነበረና የብዙ ታሪካችን መሰረት የሆነውን ባህራችን አሁን አገራችን አይገባትም ስትባል የማይበግን ኢትዮጵያዊ ካለ ምን ሊባል እንደሚችል ያስቸግራል። በሌላ አነጋገር አገራችን የተፈጥሮ ባህርዋ አጥታ ከባህር ተገፍታ ስትወጣና ባገር ደረጃ ማሰቡ ትተን ወደ አማራነት፣ ኦሮሞነትና ትግሬነት ስንወርድ በክብራችን ላይ የምት ምት ነው ብዬ ነው የማምነው።

ሌላው ድራማ ቀደም ባሉት አመታት ያለውን መንግስት ባለስልጣናት ወደ አሜሪካ አገር ብቅ በሚሉበት ሰዓትና በጠሩት ህዝባዊ ስብሰባ ስለ ወደብ ተጠይቀው ሲመሉሱልን የነበረ መልስ ብጣም የሚገርም ነበር። በጃቸው ያለ ይመስል አገራችን እንድያው የአምስት ወደብ ተጠቃሚ እንደሆነችና የራሳችን ወደብ ለምን አይኖረንም የሚለው ችግር የነፍጠኞች አስተሳሰብ ብቻ እንደሆነ በልበ ሙሉነት ሲናገሩ ነበር። የሰው ወርቅ አያደምቅ ሆነና ጂቡቲ እንካ ባቅምዋ አሁን የምታሳየን ያለው መከራ ያገሬ ሰው በሚገባ የሚያውቀው ነው። ባሁኑ ባለው የጅቡቲ መንግስት ህግ ድሮ ደረቅ እቃ ለማንሳት እስከ 3 ወር የነበረው እድል አሁን ላንድ ወር እንዲሆን በመደረጉ ወገናችን እየገጠመው ያለው ፈተና ቀላል አለመሆኑን በቅርቡ አገር ቤት ደርሶ የተመለሰ ጋደኛዬ ለኔና ለሌሎች ያጫውተን ብቻ መጥቀሱ ይበቃል።

አገር ዝም ብሎ የመጣ ሳይሆን የረጅም ጌዜ ተጋድሎና የደም ውጤት ነው።  ያለፉት ነገስታት ግዛት ለማስፋት ሲሉ የበደሉት ወገን ይኖራል፣ አለም። ይህ እውነት ነው። ታድያ ባለፈው ጉዳይ የተነሳ የረጅም ግዜ ትግልና መስዋዕትነት ውጤት የሆነው አንድነታችንን አደጋ ላይ መጣል ነው ያለብን ወይስ ያለፈው ለታሪክ በመተው እጅ ለጅ ተያይዘን የተሻለ ነገር ለማምጣት ወደፊት መራመድ? መልሱ ግልፅ ነው። ካንድነት ውጭ ሌላ ላገራችን የሚበጅ ያለ አይመስለኝም። የብሄርና ብሄረሰብ መብት የሚለው ፍልስፍና የኢትዮጵያ አንድነትን ፍፁም ማጠንከር እንጂ ማፍረስ የለበትም።

በመጨረሻም እንደ አማራ ሁኖ በተነሱት ትላልቅ ያገር ጉዳዮች ማሰብ የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ ሁኖ አላገኘሁትምና እኔም በዚሁ ጉዳይ አማራ ሁኛለሁ እላችዋለሁ። በዚሁ የሚጠይቀኝ ካለ መልሴ እየሩሳሌም ለራስሽ አልቅሺ ነው።

የኢትዮጵያ አንድነት ለዘላለም ይኑር!

ሃይለ ደስታ